# የትምባሆ ምርት አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 1003/2016 ላይ የተዘጋጀ ማብራሪያ

በምግብ እና መድሃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 ለኢትዮጵያ ምግብ እና መድሃኒት ባለስልጣን በአንቀጽ 4(4)፣ 4(17)፣ 65(5) እና 68(2) መሰረት በተሰጡት ስልጣኖች መሰረት ማንኛዉም ማሟላት ያለበትን ያላሟላ የትምባሆ ምርት ወይም አገልግሎት ያለፈበት፣ ህገወጥ ምርት ወይም አገልግሎት ላይ የማይዉል ምርት ወይም ተፈጻሚነት ያላቸውን የቁጥጥር መስፈርቶች በመጣስ የቀረበ ምርት በሰው እና በእንስሳት እንዲሁም በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስና በአግባቡ እንዲወገድ የማድረግ ሃላፊነት የተጣለበት ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 71(2) መሰረት ይህንን ለማስፈጸም የሚያስችል ዝርዝር ጉዳይ በመመሪያ እንዲያወጣ ስልጣን ተሰጥቶታል።

ከዚህም በተጨማሪ የትምባሆ ምርት እንደሚታወቀዉ በርካታ ኬሚካሎችን በዉስጡ የያዘ እንደመሆኑ መጠን ይህ የትምባሆ ምርት ሲወገድ በሰዉ እና በእንስሳ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል እንዲሁም አካባቢን በማይበክል ዘዴ እና ስርዓት መከናዎኑ አስፈላጊ መሆኑ በአዋጁ የተካተተ ጉዳይ ነዉ። የትምባሆ አወጋገድ ሲነሳ ከዚህ ጋር የሚያያዙ እንደ የትምባሆ ምርትን መለየት፣ማከማቸት፣ማጓጓዝ እና ማስወገድ ሂደቶች በህግ ዝርዝር ድንጋጌዎች ካልተካተቱበት በቁጥር ሂደት በሚፈጠር ክፍተት ምርቱ እንደገና ወደ አቅርቦት ሰንሰለት በመግባት መልሶ ጥቅም ላይ በመዋል እና በሰዉ እና በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ እና ቁጥጥር አዋጅ 1090/2010 ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የአፈጻጸም ሂደቶችን በመመሪያዉ እንዲካተት ተደርጓል።

የሚወገዱ የትምባሆ ምርቶች በአብዛኛዉ በህገወጥ መንገድ ወደ ሀገር ዉስጥ የገቡ ሲሆኑ ሌሎች በህጋዊ መንገድ ተመርተዉ ነገር ግን በትክክል ያልታሸጉ ወይም አስተሻሸጋቸዉ ህግን ያልተከተለ፣ በምርቱ ማሸጊያ ላይ ያለዉ የጤና ማስጠንቀቂያ ህግን ያልተከተለ ወይም በባለስልጣኑ ያልጸደቀ፤ በህግ ከተፈቀደዉ ዉጭ ሌሎች ፍሌቨር እና ያልተፈቀዱ ንጥረነገሮችን በዉስጡ የያዙ የትምባሆ ምርቶችም በአዋጁ መሰረት ሊወገዱ ስለሚገባ ህጋዊ ፈቃድ ያለዉ ማንኛዉም የትምባሆ ኢንዱስትሪ በባለስልጣኑ ዉሳኔ እነዚህን ምርቶች እንዲያስወግድ ሊገደድ ይችላል። በዚህም ጊዜ እነዚህ ህጋዊ የትምባሆ ምርቶች የህግ ማእቀፎች ያስቀመጧቸዉን

መስፈርቶች ባለማሟላታቸዉ ምክንያት እንዲወገዱ ሲወሰን የሚከተለሎቻዉን መርሆች በመመሪያዉ ለማካተት ተሞክሯል፡፡

በዋናነት ግን የትምባሆ ምርት ሲወገድ በሰዉ እና በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት ሳያስከትል እንዲሁም አካባቢን ሳይበክል ሊከናዎን የሚችልበትን ዘዴ በመመሪያዉ ማስቀመጥ በማስፈለጉ እነዚህን ዘዴዎች በዘርፉ ልምድ ካላቸዉ ባለሙያዎች እና የሌሎች ሃገሮችን ተሞክሮ ግምት ዉስጥ በማስገባት እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ እና ቁጥጥር አዋጅ 1090/2010 ላይ የተቀመጡ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች ቢኖሩም የትምባሆ ምርት የሚወገድበትን ሁኔታ ካለማስቀመጣቸዉም በላይ የትምባሆ ምርት ከሌሎች አደገኛ ቆሻሻ ተብለዉ ከሚመደቡ ምርቶች በብዙ መንገድ የሚለያይ እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ መመሪያዉ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህም በላይ ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ምግብ እና መድሃኒት ባለስልጣን ካጸደቃቸዉ መመሪያዎች አንዱ የመድሃኒት አወጋገድ መመሪያ ሲሆን ከዚህ መመሪያ ለትምባሆ አወጋገድ ተስማሚ የሆኑ ድንጋጌዎችን ለማካተት ተሞክሮል፡፡

መበጨረሻም የረቂቅ መመሪያዉ ለሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት በተለይም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ የአዲስ አበባ ከተማ የንጽህና ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ምግብ እና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን እንዲሁም የጉምሩክ ኮሙሽን የተወከሉ ባለሙያዎች በተሳተፉበት አዉደ ጥናት ቀርቦ አስፈላጊዉ ግብዓት ለማግኘት ተችላሏል፡፡ ስለሆነም በመመሪያዉ ላይ ያላችሁን አስተያየት በ15 ቀን ጊዜ ዉስጥ እንድትልኩልን እንጠይቃለን፡፡